# ሃይማኖትና ፖለቲካ እያጣቀሱ እስከ መቼ?

የተለያዩ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ሰብስብ የሆነው መድረክ ሰሞኑን በኣሜሪካ ድምፅ ሬደዮ ጣቢያ ይዞት የወጣው መግለጫ ኣስገራሚ ነው፡፡በፖለቲካው ማስክ ያጣውን ትርፍ **"እስቲ ወደ ሃይማኖት ጠጋ ልበልና ትንሽ ትርፍ ቢጤ ባገኝ"** ያለ ይመስላል፡፡ በሃይማኖት ሽፋን የተለያዩ መስጅዶች ደጃፍ እየተገኙ የዕለተ ኣርብ ፀሎትና ስግደት ማስተጓጎል ክፍት የስራ ቦታ ኣለ የተባሉ ይመስል የፀረ- ሰላምና የኣክራሪ ፅንፈኛ ሚእክተኞች የህዝበ ሙስሊሙን ሰላም ሚደፍረስ የየሳምንቱ ስራቸው ከሆነ ቆየት ያለ ቢሆንም የያለፈው ሰሞን ደግሞ የኢትዮጰያ ህዝብ በተጨባጭ እያያቸወና እየተጠቀመባቸው ያለውን የዕድገት፣የሰላምና የዲሞክራሲ ትሩፋቶች ጭራሽ እንደሌሉና ይልቁንም ኣሁን በኢትዮጵያ እየታዩ ያሉት የፖሊቲካና የኢኮኖሚ ችግሮች ካልተፈቱ የሃገሪቱ ህልወና ለኣደጋ የተጋለጠ ነው ለማለትም ደፍረል፡፡ የሰላም ጠበቃ ይመስል ከሰላማዊ ኣማራጭ ውጭ ያሉትንም የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሰላማዊ ትግል እንዲቀላቀሉም ጥሪውን ኣቀርቧል፡፡**ይሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ ኣለ የኣገሬ ሰው!**

ከሁሉም የሚያስገርመው ደግሞ የኢትዮጵያ ሬደራላዊ ኣንድነት መድረክ ሓምሌ 28/2005 ዓ.ም በኣዲስ ኣበባ መብራት ሃይል ኣዳራሽ በጠራው ህዝባዊ ሰብሰባ ላይ ተገኝተው የፓርቲው የኣመራር ኣባል ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ኢህኣዴግ ላለፉት 22 ዓመታት የዜጎች ሰብኣዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ኣላከበረም ብለዋል፡፡ ከ22 ዓመታት ወስጥ ዶ/ሩ የኢህኣዴግ ኣመራር ሆነው ስንት ዓመት እንደሰሩና ለሰብኣዊና ዴሞክራሲያዊ መብት እንደታገሉ ኢህኣዴግና የሚያመልኩት እግዚኣብሐር ያወቃል፡፡ ሆድ ሲያወቅ ዶሮ ማታ እንደ ማለት ይሆን? ሌላው ኣስገራሚ ነገር ደግሞ ዶክተሩ ህዝብ መብቱ እንዲጠበቅለት ሰለጠየቀ ለእስር፣ለድብደባና ለግድያ ተጋልጧል በማለት የኣዋሳ፣የምርጫ 97 ሁከትን ተከትሎ የጠፉው የሰው ህይወትና ሌሎችም ለኣብነት ጠቅሰዋል፡፡በተጨማሪም በቅርቡም ዜጎች የመብት ጥያቄ ሰላነሱ በእሰር ላይ ይገኛሉ ብለዋል፡፡በሃይማኖት ሽፋን የፖለቲካ ኣጀንዳ በማንገብ በህግ ጥላ ስር ሆነው ክሳቸውን በመከታተል ላይ ያሉት የፅንፈኛ ኣክራሪ ኣመራሮች ይፈቱ ማለት የህግ የበላይነትን ማክበር ይሆን?ኣይደለም ስርዓትና ሕግ ባለበት ሃገር ፀረ-ሰላምና ኣክራሪ ፅንፈኞች ሊፈነጩበት የኢትዮጵያ ህዝብ እንደ ማይፈቅድላቸው ኣሰረግጠው ማወቅ ኣለባቸው፡፡ ሌላው ኣስገራሚ መግለጫ ደግሞ መንግስት በሃይማኖት

ጣልቃ እየገባ ነው፣የሃይማኖት ችግር ኣለ፣ጣልቃ መግባትም ኣለ፣በዚህም ምክንያት ነገሮች ሁሉ ከቁጥጥር ውጭ እየሆኑ ነው፣በሃይማኖት የሚመጣ ችግር

በቀላሉ ሊቆም ኣይችልም ብለዋል፡፡ለማሆኑ ሕገ መንግስቱ ከረቂቅ ጀምሮ እስከ ሚፀደቅ ሰራ ሲካሄድ እኔ ኣልነበርኩም፣ ኣልተሳተፍኩም ነው የሚሉት? ወይሰ ስለ ሃይማኖት ፣ሰብኣዊ መብትና ዲሞክራሲያዊ መብት ሕገ መንግስቱ ምን እንደሚል ረስተውት ነው? ወይሰ ማወቅም ኣልፈልግም እያሉን ነው? ሕገ መንግስቱ ሰላለ እኮ ነው ደ/ር እንደፈለጉትና በፈለጉት የፖለቲካ ድርጅት ተደራጅተዉ መንቀሳቀስ ላይ የሚገኙት፡፡ በማን ላይ ቆመሽ ማንን ታሚያለሽ ይላል የኣበው ተረት፡፡

ሌላው ጉዳይ ዶ/ሩ ምን ነካቸው? የሚያሰብል ነው፡፡ መንግስት ለዜጎች ጥቃት የሚከለከሉ ሕጎች ሳይሆን ለጥቃት የሚያጋልጡ ሕጎች እያወጣ እንዲሚገኝና የፀረ–ሽብር ሕግ፣የበጎ ኣድራጎት ማሕበራት ሕግና የፕሬሰ ሕጎችን ብምሳሌነት ጠቅሰዋል፡፡ማንኛወም በሰላማዊ መንገድ እታገላለሁ የሚል የፖለቲካ ድርጅት እነዚህ ሕጎች መንግስት ሕገ መንግስቱ እንዲያከብርና እንዲሰከብር የሚያደርጉ ሕጎች በመሆናቸው መደገፍ ሲገባቸው ሲቃወሙ ይታያሉ፡፡ ታድያ የት ላይ ነው ሰላማዊነቱ? በሜጨረሻም እነዚህ ሕጎችና በሕገ መንግስቱ የሚገኙ ኣንዳንድ ህጎች እንዲሻሻሉ ወይም እንዲወገዱና በነዚህ ሕጎች የተፈረደባቸዉና የታሰሩ ሰዎች ደግሞ እንዲፈቱ ጠይቀዋል፡ይህ ዓይን ያወጣ የህዝብ ንቀትና ትምክህት ነው፡፡ ኣይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛችሁ ካልሆነ በስተቀር ሃይማኖትና ፖለቲካ ለየቅል ናቸው፡፡ከላይ እንደተገለፀው ሃይማኖትና ፖለቲካ እያጣቀሱ መኖር ያቁሙ፡

የኢትዮጵያ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሕገ መንግስት የሃይማኖት እኩልነት በግልፅ ተቀምጠዋል፡፡ መንግስት በሃይማኖት ጣልቃ እንደማይገባና ሃይማኖትም በመንግስት ላይ ጣልቃ እንደማይገባ በግልፅ ቋንቋ በሕገ መንግስቱ ሰፍሮ ይገኛል፡፡ ታድያ ዶ/ር ምን ነካቸው? ምን ኣለበት ፖለቲካውን ካልቻሉት የተማሩትን ኢትኖግራፊና ኢትኔሲቲ እንደገና ዩኒቨርሲቲ ገብተው ቢከልሱትና ፌደራሊዝምን ብኣግባቡ ቢያጠኑ! ስለዚህ ሃይማኖትና ፖለቲካ እያጣቀሱ መኖር ይብቃ!

ሜሩ ዘ/መቅለ